# ተቆርቋሪ ያጣች ሐገር

የዛሬውን አያድርገውና በቀደሙት ኢትዮጵያን ባስተዳደሩ መንግሥታት የሐገር ፍቅርን በዜጎች ልቦና ማጎልበትና የሐገር ሉዓላዊነትን ማስከበር ከማናቸውም ጉዳይ በላይ ቅድሚያ ሊሰጠውና ሊከበር የሚገባው እንድሆነ በመረዳት መንግሥት ይህንን ቅዱስ  ዓላማ ለህጻናት ገና በጨቅላነታቸው ዘመን ጀምሮ በማስተማርና  ቅድሚያ በመስጠት በየትምህርት ቤቱ ስለ ሐገራችን ትልቅነት: ስለ ሐገራችን ለምለምነት: ስለ ሕዝባችን ጀግንነት: ስለ ሰንደቅ አላማችን ክብር: ስለ አትንኩኝ ባይነታችንና በሐገራችን ጉዳይ ለሚነሳ የትንኮሳም ሆነ የአፍራሽነት ባህርያት ሁሉ ለአንዲት ሰኮንድ እንኳን የማናመነታና ለሐገርና ለወገን ክብር የሚከፈለውን ማንኛውንም አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሚያደርግ ሁኔታን ከልጅነት ጀምሮ የሐገር ፍቅርን የተላበሱ መዝሙሮችንና ዘፈኖችን በማቀንቀን በአግባቡ በሐገራዊ ፍቅር ተኮትኩተንና ታንጸን እንድናድግ መደረጉ አይካድም:: ይህ አይነት ሐገርን መውደድና  ሐገርን የማስቀደም የሐገርን ትልቅነት አጉልቶ የሚያሳይ መዝሙርና ዘፈኖች በዜጎች ስነ  ልቦና እንዲቀረጽ ማድረጉ በተወሰኑ ሐገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በመላው ዓለም በሰለጠኑትም ሆነ ኋላ ቀር ተብለው በሚመደቡትም አገሮች ውስጥ ሁሉ ህጻናት ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ እንዲያውቁትና እየዘመሩም እየዘፈኑም እንዲያድጉ የሚደረገው ያለምክንያት እንዳልሆነ ሁላችንም በውል የምናውቀው ነው:: ጥሩ ዜጋን ለማፍራት መሰረቱ ሐገርን  መውደድ እንደሆነ ግልጽ ነው: ግለሰቦችም ለሐገራቸው ታላቅ ክብር እንዲሰጡ  በማስተማር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን ማንነታቸውንና ሐገራቸውን ለተተኪው ትውልድ በሚገባ በማስተላለፍና ተተኪውም ትውልድ የአባቶቹንና የናቶቹን አደራ ተቀብሎ እሱም በተራው በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚቀጥለው ትውልድ ማውረስ እንዲችል: የአገር አንድነትና የወሰን ክብር ተጠብቆ እንዲኖር መሰረቱ የሚጣለው ገና በጨቅላነት ባለ ዜጋ ላይ እንደቀልድም እንደጨዋታም ተደርጎ አብሮት እንዲያድግ በማድረግ ለሐገሩና ለወገኑ መመኪያና አኩሪ የሆነ ዜጋ እንዲፈጠር ይደረጋል::

ዛሬ ሁላችንም ተሰደን በምንኖርበት ሐገር ልጆቻችንን ወደ መዋዕለ ሕጻነት ስንሰድ የመጀመሪያ ትምህርት ተምረው የሚመጡልን ነገር ቢኖር በመዝሙርም ይሁን በሌላ መንገድ ያሉበትን ሐገር ታላቅነት  ለሰንደቅ አላማቸው መስጠት ያለባቸውን ክብር በተጨማሪም ሕዝባቸውን ከማንምና ከምንም በላይ መውድውድ እንደሚኖርባቸው የሚያመላክት እንደሆነ እናያለን:: ይህ ሁሉ የሚደከመውና የሚለፋው  ሐገሩንና ሕዝቡን የሚወድ ትውልድን ለመፍጠር የሐገሩን ዳር ድንበር አስከብሮና ጠብቆ የሚኖር የሐገርና የሕዝብ መከታና ደጀን የሚሆን ጠንካራ ዜጋ ለማፍራት እንደሆነ ይታወቃል::

ዛሬ በኛ ሐገር ግን የሚደረገው ትውልድን የሚያኮላሽና የሐገር ፍቅር ስሜትን የሚሰልብ የወገንን ትልቅነትና ክብር የሚያናንቅ ሆኖ በምትኩ ከሐገር ይልቅ መንደርና ጎጥን: ከሕዝብ ይልቅ በቋንቋ በአምቻ ጋብቻ ላይ የተመሰረተ የጠበበ አመለካከትን የሚያራምድ የትልቋን የአንድነት ተምሳሌት ኢትዮጵያን ማንነት አኮስሶ የጎሳን ትልቅነት የሚያወድስ የራሱን ጎሳ ትልቅነትና ገናናነት የሚሰብክ የአፍራሾች: የርካሾች : የትንሾች ዘመን ተተክቶ ሐገር እንደ ሐገርነት

እንዳትቆም እየተሰበከ ትውልድና ዜጋ ጠቦ በጎጥና በመንደር እንዲያስብ ተደርጎ የታላቋ ኢትዮጵያ ጉዳይ ተናንቆ ንኡሳንን መንደረተኛነትን አጋኖና አወድሶ እየዘመረ የሚያድግ ትውልድ እንዲተካባት እየተደረገ ነው:: ያቺ የምንወዳትና የምናፌቅራት ታላቋ ኢትዮጵያችን እየጠፋች እንደሆነ ሁላችንም ዛሬ ህያው የአይን ምስክር እየሆንን የመጣንበት ጊዜ ላይ ደርሰናል::

እኛም በልጅነት ሰለሐገራችን ገናናነት : ትልቅነት: አልደፈር ባይነት: እየዘመርንና እየዘፈንን እንዳላደግን ሁሉ ለውጪም ይሁን ለሐገር በቀል ጠላት አልደፈር ባይነታችንን እንዳላቀነቀንን ሁሉ ዛሬ ይባስ ብለን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የተላለፈልንን አንድነትና ኢትዮጵያዊነት በጎጠኝነት ተክተን ወንድማችንንና እህታችንን ከመስማትና ከማዳመጥ ይልቅ ነጩ እኛን ለማጥፋትና ለመከፋፈል የኢትዮጵያዊነት መንፈስን ለመግደል ለዘመናት የዳከረበትን ሰይጣናዊ ህልም እውን ለማድረግ ስለኛ ማንነትና ምን መሆን እንዳለብን: ወዴትስ መሄድ እንደሚኖርብን: አማካሪያችንና ቅን አሳቢ: የኛን እድል ወሳኝ አድርገን በመቀበል በነጩ ህብረተሰብ ስውር ሴራ ውስጥ ተተብትበን ያጠመደልንን ወጥመድ እንደ ብሩህ ጎዳና አድርገን በመውሰድ እናትና አባቶቻችን የነገሩንና ያስተማሩንን ወደጎን በመግፋት: በማናናቅ : ሐገርንና አንድነትን በማፍረስ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን ከጋራ ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅምን: ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ጎጠኝነትና መንደረተኝነትን ስናራግብና ስናናፍስ አልፎ ተርፎም ስንሰብክ እንታያለን:: ዛሬ ሐገራችን የደረሰችበት ደረጃ እንድትደርስ አውቀንም ይሆን ባለማወቅ አሊያም በግለኝነትና በፍቅረ ነዋይ ተጠምደን ከሐገር ጠላቶች በሚጎርፍልን ሶልዲ ሕሊናችንንና ክብራችንን በመሸጥና በመለወጥ የጠላቶቻችን ዓላማ እውን እንዲሆን ለውድቀታችንና ለጥፋታችን ታላቅ አስተዋጽኦ በማበርከት የጥፋቱ አራማጆች ሆነን እንገኛለን::

ዛሬ በየ ትምሕርት ቤቱ ሕጻናት የሚማሩት ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ስለ ሐገር ፍቅር ስለሕዝባችን ትልቅነትና ሰለ ሐገራችን ለምላሜ: ስለ ሰንደቅ አላማችን ክብር ሳይሆን የሚሰጠው ትምህርት ሕጻኑ ወይንም ሕጻኗ ከየትኛው ጎሳ የመጡ እንደሆነና የኢትዮጵያዊነት መንፈስን ገዳይ ብሄራዊ ስሜትን አኮላሽ በሆነ የትምህርት መዋቅር ከመቀራረብ ይልቅ መራራቅን የሚያወድስ: ከግንባታ ይልቅ ማፍረስን የሚያቀነቅን ስርአት: አይምሮው ተሰልቦ እንዲያድግ እየተደረገ ነው:: ለዚሁም በምስክርነት ዛሬ ሕጻናት በየትምህርት ቤታቸው የሚሰጣቸው መታወቂያ ወረቀት ኢትዮጵያዊነታቸውን ገላጭ ሳይሆን ጎሳቸውን ገልጭ የሆነ ጠባብነትን አራማጅ የሆነ መታወቂያ ነው:: ኢትዮጵያዊነታቸውን ሽሮ ልዩነታቸውን የሚያገን በጎሳ ላይ ያተኮረ የአፍራሽነት የልዩነት መግለጫ ተድርጎ በተዘጋጀ ትንሽነትንና ጠባብነትን የሚያበረታታና ኢትዮጵያዊነትን ገዳይ በሆነ ሥርአት ዜጎች እንደዜግነታቸው እንዳያስቡ ይልቁንም በጎጣቸው እንዲያስቡና እንዲደራጁ የሚያበረታታ ከትልቁ ሕብረተሰብ ወጥተው ወደ ትንሹ ቤተሰብ እንዲሰባሰቡ በቅኝ ገዢዎች ለዘመናት የመከፋፈልና የማዳከም ዘይቤ እንዲዋቀሩ ቆፍጣና ሐገሩንና ወገኑን የሚወድ ዳር ድንበሩን የሚያስከብር አኩሪ ትውልድ ለማፍራት የማይቻልባት ደካማ ሐገር እንድትሆን ቀን ከሌት በምዕራባውያንና የነሱ ሎሌ በሆኑ ትንንሽ ጭንቅላት ባላቸው ጎጠኞች ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ለመሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም:: ድሮ የምናውቃት ታላቋና ገናናዋ ኢትዮጵያችን ዛሬ በባንዳ ትውልዶች በነመልስ ዜናዊና እነ ዳዉድ ኢብሳን በመሳሰሉ የንግዴ ልጆች

ኢትዮጵያዊነት ጠፍቶ ኦሮሞንርት: ትግሬነት: አማራነት: ጉራጌነት ወዘተ... እየተሰበከ ባለበት አገር ውስጥ አገርና ዳር ድንበር ተሸንሽኖ ለድርቡሾች እንኳን ሲሰጥ እንቢ ላገሬ እንቢ ለዳር ድንበሬ ብሎ አምጾ የሚነሳ ሕዝብ: ተባብሮ የሚሰራ ዜጋ ማግኘት የማይቻልባት አገር ለመሆን በቅታለች:: የነ ቴዎድሮስ አገር የነ ዮሃንስ አገር ዛሬ የድርቦሾች መናገሻ ሆኖ ማየት ለዘመናት ቅኝ ገዢዎች: አረቦችና ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች ምንኛ ሽርሽረው እንዳዳከሙንና አቅመ ቢስ እንዳደረጉን የሚያሳይ ጉልህ መስታወት ነው::

ትላንትና ኤርትራንና የአሰብን ወደብ አስወስደን አገራችንን ወደብ አልባ አድርገን ዛሬ በጎረቤት አገሮች መልካም ፈቃድ ስር ወድቀን ተለማማጭና ለማኞች መሆናችን ሁላችንንም ሊያሳዝነን: ሊያስቆጨንና ሊያንገበግበን በተገባ ነበር:: ሆኖም ግን ኢትዮጵያዊነት ስሜትን ለመግደል በተደረገው ርብርቦሽና ዘመቻ ሰለባዎች ስለሆንን አመጽን ማስነሳትና ያሻፈረኝ ባይነትን እርምጃ መውሰድ አልቻልንም:: በእርግጥም ኢትዮጵያዊነት መመታቱንና ዳግም ማንሰራራት የማይችልበት ደረጃ መድረሱን ለማረጋገጥ ኤርትራን በሸኘን በማግስቱ ከሰባ ሺህ በላይ የሆኑ ውድ የኢትዮጵያ ወጣቶችንንና አርበኞችን ካስበላ በኋላ ባድሜንና ዛላምበሳን በድል አድራጊነት ከወራሪው ኃይል ያስመለስነውን ይሂው በመሸንሸንና በማፍረስ የሰለጠነው ወያኔ አልጀርስ ላይ ሄዶ ያን ሁሉ ወጣት በከንቱ አስረግፎ መልሶ ለወራሪው ኃይል አስረክቦልን መጣ:: እውነትም ወኔያችን መሰለቡን ያረጋገጠው ወያኔ በማን አለብኝነት: በንቀትና በልበ ሙሉነት ተነሳስቶ ይሂው ዛሬ ደግሞ በጣም ሰፊና ለም የሆነውን በማእድናትና በተፈጥሮ ጸጋ የዳበረውን የምዕራቡን የኢትዮጵያ ክፍል ለድርቡሾች አሳልፎ በመስጠት ብቻ ሳያበቃ በስፍራው የተወለዱና ያደጉ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ ካባቶቻቸው የተረከቡትን: እትብታቸው የተቀበረበትን አገራቸውንና ዳር ድንበራቸውን አናስነካም በማለት ያመጹትን ያካባቢው ነዋሪዎች ከፊት ድርቡሽ ከኋላ ወያኔ ሆነው ሕዝባችንን በእሳት ረመጥ እየቆሉት ባሉበት በዚህ ፈታኝ ወቅት እንኳን : እኛ ትልቋ ኢትዮጵያ : ከናት አባቶቻችን የወረስናት ኢትዮጵያ : በዘር በጎሳ ያልተሸነሸነች ኢትዮጵያን ፈላጊዎች ነን ብለን የምንምለው እንኳን በዚህ አንገብጋቢና አገር አድን ጥሪ ላይ በአንድት መቆም ያልቻልንበት ሁኔታ በመፈጠሩ እውን ይህ ጉዳይ አንድ ያላደረገን: ይህ ጉዳይ ያላስተባበረንና ይህ ጉዳይ የወያኔ የመጨረሻው ግብዓተ መሬቱ የሚፈጸምብት አብይ ምክንያት ሆኖ ኢትዮጵያችንን ለማዳን የተከፈተልን ቀዳዳ ካልሆነ: ከዚህ የተሻለና የበለጠ ሊያስተባብረንና ሊያስተቃቅፈን የሚችል ምክንያት ይመጣል ብሎ ለማሰብ : ከዚህ የበለጠ ወያኔን ላንዴም ለሁሌም እንደ ጢስ ተኖ እንዲጠፋ የሚያደርግ ሁኔታና አጋጣሚ ይፈጠራል ብሎ ለመገመት እጅግ ያዳግታል::

በአንድ ኢትዮጵያ የሚያምን: በዘር በሃይማኖት አፍዝ አደንግዝ ያልተተበተበ: በስልጣን ጥም ያልሰከረ: ለወገኑና ለሐገሩ ከልብ የሚቆረቆርና መልካሙን የሚመኝ ንጹህ ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ: ከበስተጀርባው ቅራቅንቦ አስከትሎ የአዞ እንባ የሚያነባ አስመሳይ: አፍራሽና ገንጣዩን ኢትዮጵያዊነትን ያልተቀበለውን አቅፎ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዲሞክራሲ እታገላለሁ እያለ የሚሰብከውን የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላና እንዲሁም አንድ እግሩን መቃብር ውስጥ ከተከለና በህይወቱ መቋጫ አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ ትግሉንና ሕዝቡን ክዶ የወያኔ ጽንስ ውራጅንና የወያኔ ጭንጋፎች ጋር የሚዳራውን አለርህራሄ በማጋለጥ ሳያወላውሉ በቁርጠኝነት መምታት ካልተቻለ: ወያኔን ያክል ጠላት:

ምዕራባውያንን ያክል አሻጥረኛ : አረቦችን ያክል ታሪካዊ ጠላት : የሕዝብ ወገን መስለው ለወያኔና ለምዕራባውያን የሚያገለግሉ ቅጥረኞችን : የሲአይኤ ጥቁር አሻንጉሊቶችን: የኦነግና የኦብነግ ጉዲፋቻዎች: የወያኔ ቅምጦችንና የሻቢያ ከንፈር ወዳጆች ጥርቅም እንዲህ በዋዛ ማሸነፍና ኢትዮጵያን ማዳን: ኢትዮጵያ እንደ ሐገር መቀጠል እንድትችል ማድረግ ይቻላል ብሎ ማስቡ ላም አለኝ በሰማይ ይሆናልና አገራችንንና ሕዝቡን ከዚህ ውስብስብ የጠላት መረብ ለማውጣት ካስፈለገ ያለው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው:: እሱም የአላማ ጽናት ያለውና ለመስዋዕትነት በቁርጠኝነት የተዘጋጀውን በአንድ ላይ  አሰባስቦ የአላማውን ጽናትና እምነቱን ባንዳውና ሆድ አደሩ ሊቋቅውመው ስለማይችል ወገበ  ሰባራውንና ሀሞት  የለሹን : የሚያራግበውንና የሚያናፍሰውን ወንዝ ለማያሻግር ጫጫታው ጆሮ ሳይሰጡ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች ዛሬ መሰራት ያለበትን ዛሬውኑ መስራት ካልተቻለ ነገ መራቁ ብቻ ሳይሆን ሊያመጣም የሚችለው ገጠመኝ ስለማይታወቅ ቀበቶን ጠበቅ አድርጎ መደረግ ያለበትን በሰዓቱና በወቅቱ ይደረግ:: ሐገርን በተመለከተ ለይሉኝታ ቦታ ልንሰጠው አይገባምና በግራና በቀኝ ሆነው ከሚያዋክቡና ጩኸት ለሚያበዙት ቁብም ሳይሰጡ እራስን ከነዚህ እንካ ሰላንቲያና አተካራ አግልሎ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እጅና ጓንት በመሆን ይሄንን ጸረ ኢትዮጵያ የሆነን የወያኔ አሜኬላ ጭራውን የቋጠረበትን ተማምኖ ሕዝብን የናቀ  እኩይ: እንኳን በርጥባን ዱላ ከጓሮም በሚዘነጥሉት ቆመጥ ቢሆን የሕዝብ አመጽ መግታት እንደማይቻል ትምህርት ሊሰጠው ይገባልና በአንድ ልብ ሆነን ሕዝባችንን ተንተርሰን ጎረቤትም ሳንሄድ በሐገራችን ተራራ ታጅበን በሸለቆዎችና በሕዝባችን መሀል መሽገን በአንድነት ብንነሳ ቃላችንን በተግባር ብንተረጉመው የድል ቀን እኛ ከገመትነው በላይ የቀረበ ንደሚሆን እሙን ነው::

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ታዛቢው